ቅድስት - የዐቢይ ጾም ሁለተኛ ሳምንት

የዐቢይ ጾም 3 ምዕራፎች ሲኖሩት እነርሱም ዘወረደ /ጾመ ሕርቃል/፣ የጌታ ጾም እና ሕማማት ይባላሉ። ጾመ ሕርቃልን ባሳለፍነው ሳምንት የተጾመው ሲሆን ‹የጌታ ጾም› የሚባለው ከቅድስት ሰኞ እስከ ሆሳዕና ዋዜማ ዓርብ ድረስ ያለው 40 ቀን ነው። ቅድስት የዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያ የዐብይ ፆም ደግሞ ሁለተኛ ሳምንት ነው። «ቅድስት» ማለት የዘይቤ ፍቺው «የተመረጠች፣ የተለየች» ማለት ሲሆን ምስጢራዊ መልእክቱ ግን የምስጢረ አድኅኖት ታላላቅ ሥራውን ለመጀመር መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዳመ ቆሮንቶስ ገብቶ ከቆመ ሳያርፍ፣ ከዘረጋ ሳያጥፍ የጾማት የአርባው ቀንና ሌሊት ልዩ እና ክብርት የሆነች ጾም የምትጀመርበትን ሁለተኛ ሳምንት ከልብ ያሳስበናል። ስያሜውን የሰጠው ኢትዮጵያዊው የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ሲሆን የምናገኘውም ‹‹ፆመ ድጓ›› በተባለው ድርሰቱ ውስጥ ነው። ከዚህ ሰንበት ዋዜማ ጀምሮ ስለ ዕለተ ሰንበት ቅድስና ይዘመራል፤ ቅድስት ቤተ-ክርስቲያናችንም ስለ ቅድስና ልጆቿን ታስተምርበታለች። በቅዳሴ ጊዜ የሚሰበከው ምስባክ፤ የሚነበቡ መልዕክታት፤ የሐዋርያት ሥራ እና ወንጌሉ ሁሉ ስለ ቅድስና የሚያስተምሩ ናቸው።
በዚህ ሳምንት የሚሰበከው ምስባክ ይህ ነው፡- መዝ 95፡ 5

እግዚአብሔርሰ ሰማያተ ገብረ ፤ **እግዚአብሔር ግን ሰማያትን ሠራ፤**

አሚን ወሰናይት ቅድሜሁ ፤ **ምስጋናና ውበት በፊቱ ነው፤**

ቅድሳት ወዕበየ ስብሐት ውስተ መቅደሱ።። **ቅዱስነትና ግርማ በመቅደሱ ውስጥ ናቸው።።**

‹‹ቅዱስ›› ማለት ልዩ፣ ክቡር ማለት ነው። እግዚአብሔር አምላካችን በባሕሪው ቅዱስ ነው። ይህም ቅድስና ከማንም ያላገኘው የባሕርይ ገንዘቡ፤ እርሱም የቅድስና ምንጭ ነው። መጻሕፍት እና ነቢያትም የባሕርይ ቅድስናውን በመመስከር ‹‹ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ›› እያሉ ያመሰግኑታል። /ኢሳ 6፡13፤ 40፡25 ራዕ 15፡4፤ 1ሳሙ2፡ 23/ እኛም ቅዱስ ልጁ በሥጋ ተገልጦ እንዳስተማረን በየዕለት ጸሎታችን ‹‹ስምህ ይቀደስ›› እንለዋለን። ‹‹ቅዱስ›› የሚለው ቃል ለዕለታት፡ ለመላእክት፡ ለሰዎች፡ ለቦታ፡ ለዕቃ ... ቢቀጸልም ቅድስናቸው በባሕርይው ቅዱስ ከሆነው ከእግዚአብሔር የተገኘ ነው እንጂ የባሕሪያቸው አይደለም። ይህም የጸጋ ቅድስና ይባላል። እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ በመልኩና በምሳሌው አክብሮ የፈጠረንን እኛም ቅዱሳን እንድንሆን ይፈለጋል። ቅዱስ ጴጥሮስ ‹‹ዳሩ ግን እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ›› ተብሎ ስለተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተም ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ›› ያለን ይህንን ሲያስተምረን ነው። እኛስ፤ እግዚአብሔር ደስ ብሎት የሚቀበለውን ሕይወት ለመኖር እንፈልጋለን? ለመሆኑ ይህ ሊሆን የሚችለው እንዴት ብንመላለስ ነው? መልሱን ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ‹‹....በዓለምም ከሚገኝ ርኩሰት ሰውነትን መጠበቅ ነው።።›› በማለት ይመልስልናል /ያዕ 1፡2627/። በዓለም የሚገኘውን ርኩሰትም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹የሥጋ ሥራ›› በማለት ገልጾታል። ‹‹እርሱም *ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖት ማምለክ፣ ሟርት፣ መጣላት፣ ኩራት፣ የምንዝር ጌጥ፣ ቅናት፣ ቁጣ፣ ጥርጥር፣ ፉክክር፣ ምቀኝነት፣ መጋደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት* ይህንም የመሰለ ሁሉ ነው፤ እነዚህን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግስት አያዩምና›› /ገላ5፡19/። በክርስቶስ ደም የተቀደሰና የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነውን ሰውነታችንን በሕይወታችን ሁሉ በዓለም ከሚገኝ ርኩሰት መጠበቅ የሰማያዊ ርስት ወራሾች ያደርገናል። የምግባርና የሃይማኖት ፍሬ አፍርተን ብንገኝ ለቅድስና የጠራንን እግዚአብሔርን ደስ እናሰኝዋለን፡ ፡ እነዚህንም ነገሮች ቅዱስ ጳውሎስ **‹‹የመንፈስ ፍሬዎች››** ብሏቸዋል። እነርሱም ‹‹ *ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ምጽዋት፣ ቸርነት፣ እምነት፣ ገርነት፣ ንጽሕና*›› ናቸው /ገላ 5፡22/።
እንግዲህ ቅድስናችን በኑሮአችን ሁሉ እንዲሆን ታዘናልና /1ጴጥ1፡15/ በተሰማራንበት የሥራ መስክ ፣ በማኅበራዊ ኑራአችን፣ በምንበላው ምግብ፣ በምንለብሰው ልብስ፣ በንግግራችንና በመሳሰለው ሁሉ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኘውን በማድረግ እግዚአብሔርን በሚሞት ሥጋችን እናክብረው። የኃጢአትንም ሸክም ሁሉ ከእኛ አስወግደን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግስት እንሩጥ። ሥጋዊ ምኞታችንንና መሻታችንን ሰቅለን፤ አሮጌው ሰውነታችንን አስወግደን፤ ንስሐ ገብተን፤ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ተቀብለን በቅድስና እንድንኖር ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር !!!